# “ሕዝብ ወደፊት ይወስናል” ማለት
# ማንም አይችልም

*ከጋቢሳ ሌንጮ ወሊጋ*

ይኸ ፁሑፍ ሰበብ ሆኖ ዝነኛው ገሞራውንና አሉላን አምታታ።

ኃይሉ ገሞራው መቼም ፈንዘክ እያለ ፅሑፍ እየዘራራና ግጥም እየኰተኰተ እንደ ሰው - ሰልቅጥ ኮሮኮዳይል ተፈርቶና ተደንቆ መላ እድሜውን ለኢትዮጵያ መድቦ በትግልና በስደት እየተፋለመ ያለ ግዙፍ አገር ወዳድ ፖለቲከኛ ነው።

ገሞራው በጣም ደስ የሚል፣ ጨዋታው የማይጠገብ፣ ለዛና ደርዝ ያለው፣ የአማርኛውን ግጥሞች ሳናነሳ በእንግሊዘኛ ግጥሙ ብቻ በመላ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መሥራች መሪዎች የተመሰገነ በተለይም በፕሬዚዳንት ገማል አብዱል ናስርና በፕሬዚዳንት ክዋሜ ንክሩማ በጣም የተደነቀ ሊቅና የመጠቀ ክብር ኢትዮጵያዊ ነው።

አሉላ በተቀዋሚ ጎራ ያለውንና አሳሳቢ የሆነውን የተረዳ ነው። ይህ ደስ ሲለን፣ ብሔር/ብሔረሰብ እያለ የትርምስ ምንጭ የሆነውንና አገር ያጠፋውን የወያኔና የስታሊኒስት ቋንቋ አልተው ማለቱን ደግሞ ልብ ብለናል።

በባዕድ ቲዌሪና ፍልስፍና ማጥ ውስጥ የዘቀጡ፣ የላሸቁና የአፍራሽ ኃይሎች ቅጥረኛ የሆኑ ግለሰቦችም ይህንን የስታሊኒስት ቋንቋ እየተናገሩና መመሪያ እያደረጉ ኢትዮጵያዊነትን በመርገጥና በመጫን አገሪቱንና ሕዝቧን ችግር ላይ ጥለዋል። **በአገር ክልል ውስጥ ያለ ሁሉ በኢትዮጵያዊነቱ አንድ ሕዝብ ነው።** በአንድ ሕዝብነቱ ደግሞ መንግሥት አቋቁሞ ለሰባት ሺህ ዓመታት የኖረ ከቻይና ቀጥሎ በዓለም ላይ ሁለተኛው በታሪክ የታወቀና የተደነቀ ሕዝብ ነው። አገር ላጠፋ አመለካከትና ቋንቋ ከእንግዲህ ቦታ ሰጥተን በኢትዮጵያ ምድርና በሕዝባችን ላይ ሌላ ትርምስና ስህተት አይደገምም።

“ሕዝብ ወደፊት ይወስናል” እያሉ ለፍርስራሽ ቅጥረኛ ገንጣዮች ተስፋ መስጠትና የወያኔ/ ሻቢያን ኢትዮጵያን የማፍረስና ሕልውና የማሳጣት ተልዕኰን ማሳካት ማንም አይችልም።

አሉላ ካሳሰበው ውግዘት ጋር ሻገር ብለን “ሕዝብ ወደፊት ይወስናል” እያሉ ውድ አገራችንን ለድርድር፣ ለቅርጫና ለሕልውና ማክተም ያቀረቡና ለዚህም ተግባራዊነት የኀብረት ሰነድ በጋርዮሽ ፈርመው የሚንቀሳቀሱ ሁሉ እንዲሁም እገዛና አመራር እየሰጡ ያሉት ወያኔና ሻቢያ ጭምር በአህዳዊ እናት አገርና በማይገሰሰው ሉዓላዊ ሕልውና ላይ ክህደት እንደፈጸሙ ታውቆ በትሪዘን፣ሽብርተኛነትና በጐጠኛ ጄኖሳይድ ወንጀሎች

በብሔራዊ ደረጃ፣ በተባበሩት መንግሥታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየታደኑና እየተለቀሙ ለፍርድ የሚቀርቡበት ጊዜ ቁልጭ ብሎ ተቃርቧል።

አገር ወዳዱ ኃይል ምን ያህል እንደቆረጠ፣ እንደተዘጋጀና በተጠንቀቅ ላይ እንዳለ ከግዝፈቱ የተነሳ መለኪያ የሌለው እልፍ ነው። ይህ የሕቡዕ ኃይል የሠማይ አእዋፍና የምድር ሠራዊት ሊያውቁት በማይችሉት ቀን ከዳር እስከ ዳር በኢትዮጵያ ላይ እንደ ሱናሜ ፈስሶ አገሪቱን ቸንክሮ የያዛትን ሁሉ በጣጥሶ ነፃ ያደርጋታል።

በጋራ ኅብረት እስካልታቀፉ ድረስ በራሳቸው መተማመን ያቃታቸው የአንድነት ኃይሎች ሁሉ ከመሸማቀቅና በራስ አለመተማመን የፈሪ ጉድጓዳቸው በጊዜ ወጥተው አገር ወዳዱን ኃይል እንዲቀላቀሉ እየመከርን ኋላ ሩጦ መድረስ አስቸጋሪ እንደሚሆን አበክረን እናሳስባለን።

*የአገር ጠላቶች ሁሉ*
*በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል*
*ይወድማሉ!*